# ዝንጉርጉሩ ሆይ!

የሰው ልጆች ንጋት፣ የፍጥረት መባቻ
የቋንቋ፣ የጐሣ፣ የዘር መከማቻ
ተራራ፣ ሸለቆ፣ የሩቅና ቅርቡ
ከሰሜን፣ ከደቡብ፣ ከምስራቅ፣ ምዕራቡ
ኣርብታ፣ ኣብዝታ፣ ቀላቅላ መውለዱ
ኻብታምና ድኻ፣ ፈሪና ደፋሩ
ክርስትያን እስላሙ፣ ቀይና ጥቁሩ
እናቴ ኢትዮጵያ ዝንጉርጉሩ ሆይ!
ጸንታ ትኖራለች በጥንቱ መንገዱ

ጠላቶችሽ ዙርያ ከብበው ቢፎክሩ
ፍጻሜያቸው ከንቱ ይታያል ባጭሩ
ለጦር መዘጋጀት ተገቢ ቢሆንም
ፍርሓት ኣይግባብሽ፣ ምንም ኣትሆኝም
ኣርብተሽ፣ ኣብዝተሽ፣ ቀላቅለሽ መውለድሽ
ልግመኛው፣ ታታሪው፣ መጥፎውና ጥሩ
ጭምት፣ ልክስክሱ፣ ረዥምና ኣጭሩ
እናቴ ኢትዮጵያ ቻይ ነው፣ ስፌ ሆድሽ!
ጸንተሽ ትኖሪያለሽ በሰላም መንገድሽ

እግዜር ይጠብቅሽ ከእኩይ፣ ከሓጥኣን
በነብያት፣ በሸኾች፣ በቅዱሳት ጻድቃን
ጥንት የተነገረው ክሱት ሆኗል ሕልሙ
ልጆችሽ በዓለም ይልሙ፣ ይለምልሙ
ኣርብታ፣ ኣብዝታ፣ ቀላቅላ መውለዱ
መልከ ጥፉ፣ ቆንጆ፣ ትሑትና ኩሩ
ትዕቢተኛ፣ ደረቅ፣ ወይም ዓይን-ኣፋሩ
እናቴ ኢትዮጵያ ዝንጉርጉሩ ሆይ!
ጸንታ ትኖራለች በሰላም መንገዱ

መቸኮል የላትም፣ ኣጉል መርበትበት
ሁሉን ኣስተውላ በትዕግሥት ማየት
ጅሃድ የሚያውጁ ልክፍቶቹ ኣሉ
እንደ ኣመጣጣቸው ሁሉም ይሸኛሉ
ኣርብተሽ፣ ኣብዝተሽ፣ ቀላቅለሽ ወልደሻል
ኣብረው የሚዘምቱ፣ ኣብረው የሚኖሩ

ጠላትን ሲወጉ እጅግ የሚያስፈሩ
ደጓ፣ ሆደ-ሰፊ፣ እናት ተብለሻል
የኢትዮጵያ ኣምላክ ሰርክ ይጠብቅሻል

ዓለም የማይገባው ረቂቅ ምስጢርሽ
ዝንጉርጉር ልጆችሽ ከጉያሽ ዐቅፈሽ
መቸም ትኖሪያለሽ በነፃነትሽ
ለዚህ ነው ጠላቶች የሚቀኑብሽ
ኣርብታ፣ ኣብዝታ፣ ቀላቅላ ወልዳለች
ሊቅና ደንቆሮ፣ መሃይም፣ ምሁሩ
ባሕሩን ኣሻግረው ሩቅ ያሚያባርሩ፣
እናቴ ኢትዮጵያ ሆደ-ሰፊ ኣለች
በሰላም መንገድዋ ጸንታ ትኖራለች!

ገ/ኢ. ጐርፉ።